# የእነ ዶ/ር ብርሃኑና የወይዘሮ ብርቱካን ቡድን ያልተሳካው ድብቅ ተልዕኮ

ከኃይለ ልዑል ግርማ
ዋሽንግተን ዲ.ሲ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ይመሩኛል ብሎ እምነቱንና ድምጹን ሰጥቲቸው የነበሩት የቅንጅት መሪዎች ወደ ቃሊቲ እስር ቤት ሲጣሉ በውስጥም በውጭም ያለው ኢትዮጵያዊ ለማስፈታት ያላደረገው ነገር አልነበረም፡፡ አዎን ብዙ መስዋዕትነት ተከፍሎበታል፡፡ ሆኖም ግን በቃሊቲ እስር ቤት ምን ሲካሄድ እንደነበር በውጭ ያለው ሕዝብ ብዙም አያውቅም ነበር፡፡ ነገሮች ሁሉ ቁልጭ ብለው መውጣትና መታወቅ የጀመሩት ከተፈቱ በኋላ ነበር፡፡

በቃሊቲ እስር ቤት እያሉ የቀድሞው የአሜሪካ አምባሳደር የነበረችው ቪኪ ሀድልሰን በአንድ በኩል እነ አየለ ጫሚሶን በገንዘብ እየደለለች ቅንጅትን ለመከፋፈል ስትጥር በሌላ በኩል ከነዶክተር ብርሃኑ ነጋ ጋር ደግሞ ሌላ ጨዋታ ይዛ ነበር፡፡ የተለየ አይደለም የቅንጅትን መሪዎች በመከፋፈል በከፊል እንዲለቀቁ እነ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ደግሞ አክራሪ ተቃዋሚ ተብለው ወህኒ እንዲቆዩ ለማድረግ ነበር፡፡ እነ ብርሃኑ ነጋን ለማስፈታት ቀደም ብሎ ተሞክሮ ከዚያም በእነ ያማሞቶም አማካኝነት ለማስፈጸም ነበር ሆኖም ግን ጥቂቶች ተለይተው ቢለቀቁ የሚገጥማቸው እጣ የልደቱ አያሌውን አይነት ስለሆነ ከዚያ ይልቅ የሚሻለው መሪዎቹን መከፋፈሉና ሁሉም ከተለቀቁ በኋላ ቅንጅት ተጠናክሮ እንዳይቀጥል ለማድረግ የታቀደው ይበልጥ ተቀባይነት አግኝቶ የውስጥ ሥራ ተጀመረ፡፡

እንደሚታወቀው በውጭው ያለው የቅንጅት ደጋፊ ሊከፋፈል የቻለበት ዋናው የችግሩ መንስኤው ከቃሊቲ እስር ቤት እነ ብርሃኑ ነጋ የሚሰጡት መመሪያ ነው፡፡ በውጭ እንደ እነ አንዳርጋቸው ጽጌና ብርሃነ መዋ የመሳሰሉ የጠላት መሳሪያዎች አማካኝነት ተሳካ ባይባልም ከፍተኛ መዳከምንና መከፋፈልን ያስከተለ የጥፋት ስራ ተሰርቷል፡፡ በጄንዋሪ 2006 ለሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ስብሰባ ላይ እንግዳ የነበረው አንዳርጋቸው ጽጌ ከአምስት ወር በኋላ ከብርሃነ መዋ ጋር በመሆን ያልተጠበቀ ችግር ፈጠረ፡፡

እነአንዳርጋቸው ጽጌና ብርሃነ መዋ የፈጸሙት የጥፋት ተግባር ብዙ ተብሏል ብዙ ተነግሯል፡፡ መታወቅ ያለበት የጥፋታቸው መንገድ እንዲሳካ የተጠቀሙበት ሁለት መንገዶችን ነው፡፡ አንደኛው የብርሃነ መዋ ስልት መሳሪያ የሆኑት ካድሬዎቹን የመረጣቸውና የመለመላቸው በአካባቢ ልጅነት መሆኑ የተለመደ የወያኔ የመከፋፈያ ስልት ነው፡፡ ሸዋ፣ ጎጃሜ ወዘተ… የሚለው የወያኔ እንጂ የቅንጅት መርሆና ራዕይ አይደለም፡፡ በዚህም ወጥመድ ውስጥ የገቡለት ጥቂት የጎጃሜነት ስሜታቸው ከኢትዮጵያዊነታቸው የሚበልጥባቸው ጠባቦችና ደካሞች አሳፋሪዎች አማካኝነት ነው፡፡

ሌላው አንዳርጋቸው ጽጌ ካድሬዎቹን የሚመለምላቸው በጣም ገንዘብ የሚወዱና ወንጀል መፈጸም ባሕሪያቸው የሆኑ ሰዎችን በመምረጥ ነው፡፡ ወንጀለኛ ስለነበሩ ሌላ ወንጀል ለመፈጸም ምንም ወደ ኋላ የማይሉ ናቸው፡፡ እንዲሁም መለፍለፍ የሚችሉ አፈኞችና ጥቅም የሚገዛቸውን መምረጡ ለገንዘብ ብለው ኢትዮጵያዊውን ክፍል የማዋረድ፣ ስም የማጥፋትና የማሰበርገግ ተግባር ሲፈጽሙ ትልቅ አኩሪ ስራ የፈጸሙ ይመስል ሲናገሩት በኩራት ነው፡፡ ልብ ብላችሁ የእነ አንዳርጋቸው ጽጌን ካድሬዎች ታሪክ ተከታተሉ፣ ጠይቁ፡፡ የወንጀል ሪከርድ ያለባቸው ናቸው፡፡ የሲያትሉ፣ የዲሲው፣ የቶሮንቶው፣ የካልጋሪው፣ የአትላንታው ወዘተ…

ወደ አገር ቤት እንመለስ፤ እነ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ውስጥ ውስጡን ይሰሩት የነበረው ሴራ ራሱን የቻለ ታሪክ ነው፡፡ ከእስር ቤት የወጡ ሰዎች በሰጡት መረጃ መሰረት፤ መፈንቅለ ስልጣን የማካሄድ ስራ የተጀመረው ከአንድ ዓመት በፊት ነበር፡፡ ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልን ከሊቀመንበርነታቸው እንዲለቁ መልዕክተኛ ሲልኩ ውስጥ ውስጡን የራሱን ተከታዮች በጥቅም፣ በገንዘብ ኃይል፣ በማስፈራራት፣ በብላክ

ሜል በማድረግና ስልጣን እንደሚሰጣቸው ተስፋ በመስጠት ሲያጠናከር መሰንበቱ የአደባባይ ምስጢር ነው:: የሚቀጥለው እርምጃ ደግሞ ኮሌክቲቭ ሊደርሽፕ የሚል ፈሊጥ በማምጣት ሕዝብና ፓርቲው የመረጣቸውን መሪ ለመገልበጥ የታቀደ ሴራ ነው::

እነ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ቀዝቀዛና ጭለማ ክፍል ለብቻቸው ሲታሰሩ፣ እስር ቤት ውስጥ እንኳን ቆመው እንዳይራመዱ ቁመቱ አጭር የሆነ ክፍል ውስጥ ሲወረውሩዋቸው፣ አደገኛ ወንጀለኞች ያሉበት ክፍል ሲወስዷቸው፣ ብርሃኑ ነጋ አንዴ ሰፋ ያለ ክፍል ሌላ ጊዜ አመቺ የሆነ ክፍል ሲያቀዩት፣ ማታ ማታ ትፈለጋለህ እየተባለ ውጭ ይወጣ እንደነበር፣ በስልክ ከእነአንዳርጋቸው ጽጌ ጋር ይገናኝ እንደነበር ሲታወቅ ቃሊቲ የቆየበት ጊዜ በእስረኛ ስም ትልቅ የወያኔን ተልዕኮ የሚፈጽምበት ቦታ እንደነበር ግልጽ ሆኗል:: አንዳርጋቸው ጽጌም ይህንን ሲያረጋግጥ የቃሊቲ እስር ቤት ጉዳይን ለእኔ ተዉት እኔ አክስስ አለኝ ብሎ ሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ስብሰባ ላይ ሲናገር አዳማጩን ሁሉ አስደንግጧል::

ለመሆኑ ወደ አሜሪካ የመጣው የአመራር ቡድን ባጣዳፊ ተቻኩሎ ለመውጣት የሮጠበት ምክንያት ምንድነው? ተልዕኮው ምን ነበር? ከመጣ በኋላ ምን ሰራ? የሚለውን በአይናችን ያየነው ስለሆነ እኛ እንገመግመዋለን እንጂ እንዲህ ነው እንዲያ ነው ሊሉን ሊደብቁን ሊዋሹን አይችሉም::

የእነ ብርሃኑ ነጋ ሴራና ጉድ መቼም ተወርቶም አያልቅ:: ከቅንጅት አመራር አመራረጥ ጀምሮ እስከ የሕዝብ ተቃውሞን ማዳፈን፣ ከነጻነት ጎህ ሲቀድ መጽሐፍ እስከ የቅንጅት ኢንተርናሽናል ሊደርሽፕ ምስረታ፣ ከኮሌክቲቭ ሊደርሽፕ አመጣጥ እስከ ዱባይ ቢችና የአሜሪካ ጉዞ ጉዳይ ቢዘረዘር ከእስር ቤት ሆኖ ጻፈው ከተባለው መጽሐፍ በላይ ገጾች ያሉት መጻፍ ይቻላል::

ለመሆኑ ሩጫቸው ለምን ነበር? ቢባል ለሁለት ነገር ነው:: አንደኛው የእነአንዳርጋቸው ጽጌንና የሌሎቹን ካድሬዎቻቸውን ሥራ እውቅና ለመስጠትና ለማጠናከር፣ ከሕዝቡ ላይ በቅንጅት ስም ገንዘብ ለመሰብሰብ እና እራሳቸውን ለማዝናናትና ለማስደሰት ነው::

ሕዝቡን ለማመስገን፣ በድጋፍ ድርጅቶች መካከል የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት፣ ገንዘብ ለማሰባሰብና በውጭ ያለውን የድጋፍ ድርጅት ለማጠናከር ብለው ነበር ካገር ቤት ከመነሳታቸው በፊት የተናገሩት:: ለመሆኑ ይህንን ፈጽመዋል ወይ? ብለን ብንጠይቅ በጭራሽ ይሆናል መልሱ::

ይህንን በትክክሉ ለማስቀመጥ ያህል፣

1ኛ. ከመጀመሪያውም ላዕላይ ምክር ቤት በወሰነው መሰረት እያሉ በተደጋጋሚ ሲጠቅሱትና ትክክለኛ አሰራር የሰሩ ቢያስመስሉም ስህተት መሆኑን የሚያሳየው ከ60 ላዕላይ ምክር ቤት ውስጥ የተሰበሰቡት 22 ብቻ መሆናቸው ውሳኔያቸው የማይሰራ መሆኑን ያረጋግጣል::

2ኛ. ነጻና ገለልተኛ የተባሉት ሶስት የአስተናጋጅ ኮሚቴ አባላት የተባሉት በእነ አቶ ደበበ እሸቱ አማካኝነት የቀረቡ ሲሆን ሁለቱ ከእነ አንዳርጋቸው ጽጌ ጋር በቅርብ ሲሰሩ በተለይ አቶ ታማኝ በየነ በረቀቀና በተቀነባበር መንገድ ተመቻችቶ የቀረበ ሲሆን ታማኝ ለማን ይሰራል? የኢትዮጵያ ቴሌቭዢን ኔትዎርክ በማንና እንዴት ተቂቂመ? የሚለው ወደፊት የሚጋለጥ ስለሆነ ሌላ ጊዜ እመለስበታልሁ:: ባጭሩ ከአንድነት ወገን ሳይሆን ከጠላት ወገን ነው:::: ታማኝ በየነ እንደስሙ ሳይሆን ከዳኝ ቢባል ትክክለኛ ባህርዩን ይገልጻል::

3ኛ. አሜሪካ በመጡ ሳምንት ሳይሞላቸው እነ ብርቱካን የቅንጅቱ መሪን ከድተው ኮሌክቲቭ ሊደርሽፕ እንጂ መሪ የለንም ያሉበት፣ በአስር ደቂቃ ርቀት ላይ ሆነው መሪያቸውን ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆኑ አፈንጋጮች፣ ለይስሙላ ያህል አንድና ሁለት ቀን ሲቀረው ሊቀመንበሩ በማያውቁት ፕሮግራም ላይ ስብሰባ ይሳተፉ እያሉ የግብር ይውጣ ጥሪ ማቅረባቸው፣ ከመጀመሪያው ጀምሮ በእነ

ብርሃነ መዋ እና አንዳርጋቸው ጽጌ ፕሮግራም እንጂ የልዑኩን መሪ እውቅና ያገኘ ስብሰባ አለማድረጋቸው ዓላማቸው ምን እንደሆነ አስመስክረዋል።

4ኛ. በየቦታው ጉሮ ወሸባዬና በሊመዚን መንሸራሸራቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዲረሱት አድርጓቸዋል የሚያሰኘው አንዳችም ቦታ ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ሰቆቃ ያነሱበት ያስታወሱበት ቦታም አልነበር። እነ ብርቱካን እርሷን ከወያኔ እስር ለመከላከል የተገደሉትን የሰፈርዋን ሰዎች ያስታወሰችበት የጠቀሰችበት ቦታ የለም። በዳላስ ኤርፖርት ለአምስቱ ሰዎች ስድስት ትላልቅ ሊመዚኖች ሲጠብቃቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ችግር አስረሳቸው፣ ግብዣውና ጭፈራውና እስክስታውና ሆታው ፎቶ መነሳቱና ልብስ ሽመታው ስራ ብዙ አድርጎ አከረማቸው። እንዲህም አድርጎ መሪ የለም።

5ኛ. በየትኛውም ከተማ የተለያዩትን የድጋፍ ድርጅቶች ለማስማማት፣ ችግራቸውን ለመቅረፍ ያደረጉት ሙከራ የለም። ለአብነት ያህል በዚህ ከተማ ያሉትን ችግር ያለባቸውን የድጋፍ ድርጅቶች አስማማን ወይም ችግር ፈታን የሚሉት ነገር የለም። ከአገር ቤት ሆነው ግንኙነት ያደረጉት ሲመጡም የተቀበሏቸው፣ በሊመዚን ያንሸራሸሯቸው የእነ አንዳርጋቸውና የብርሃነ መዋ ካድሬዎች ናቸው። ለረጂም ጊዜያት ድጋፍ ሲሰጡ የነበሩ የድጋፍ ድርጅቶች እንዳልነበሩና እንደማያውቋቸው ሆነው ሁለት ወር ተቀምጠው አሳልፈዋል። ባጭሩ ለወያኔ ከሚያደገድጉ፣ ለጥቅም ካደሩ፣ ጸረ ኢትዮጵያ አቂም ካላቸውና ከወንጀለኞች ጋር ሲዶልቱ ሲጨፍሩ ከርመው ሄዱ ቢባል በትክክል ስራቸውን ይገልጸዋል። በበረዶ፣ በከፍተኛ ብርድ፣ በዝናብ፣ በጸሐይ እየተሰለፈ ሲጮህላቸው የነበረውን የውጭ ነዋሪ ጨርሶ ረስተውታል። በየከተማው የወጣባቸው የተቃውሞ መግለጫና የተቃውሞ ጥያቄዎች ለመጥቀስ ያህል በሲያትል፣ ላስቬጋስ፣ አትላንታ፣ ሎስ አንጄለስ፣ ቶሮንቶ፣ ኦክላንድ፣ ኦሀዮ የወ ጡት የተቃውሞ መግለጫዎች ማስረጃ ናቸው። እንዲያውም ጎረቤታችን ካናዳ ውስጥ በቶሮንቶ ከተማ ለወይዘሮ ብርቱካን የቀረበላት አፋጣጭ ጥያቄ የመጣችበትን ቀን ሳያስረግማት እንዳልቀረ ሰዎች አጫውተውኛል። ሌላው በፈርሱ የሚያጓራው የአቶ ደበበ እሸቱ ፈጽሞ የመሃይምነትና የአላዋቂነት አባባል ሁላችንንም አስቆናል። አሳፍሮናል። "ቅንጅት ሞቲል እና ወራሽ ነን የምትሉ ቅረቡ" የተባለ ይመስል የቅንጅት ሎጎ ወይም አርማ የእኔ የደበበ እሸቱ የግል ሀብት ነው። ማንም በግሉ ሊያስመዘግብ አይችልም እንዲያውም ከስሼ ካሳ አገኛለሁ ሲል መደመጡ ሰውዬው በትክክል ያስባል ወይ ወይስ ጤነኛ አይደለም ያሰኛል። የቅንጅት አርማ ወይም ሎጎ የቅንጅት ነው። የደበበ እሸቱ አይደለም። በእርሱ ሰበብ እከራከራለሁ በማለት አሜሪካ ወይም ካናዳ ለመቆየት ያሰበው ከሆነ ያው የለመደበት የጥቅም ጉዳይ ዛሬም ማንጸባረቁ እጅግ ያሳፍራል። ቅንጅት ምን ዓይነት ሰዎችን ይዟል? እነዚህ ናቸው ወይ መሪዎቻችን ስንላቸው የከረምነው? ያስብላል። በአጭሩ በጣም በጣም አሳፋሪ የመሀይም አባባል በመናገሩ አፈርኩለት።

6ኛ. ሌላው በጣም ያስደነገጠንና ያሳፈረን ነገር ቢሆን ከቅንጅት ራዕይና ዓላማ ውጭ የጠባብነትና የዘረኝነት መንገድ ላይ ያተኮሩበት ሁኔታ የሰዎቹ አቂም ምን እንደሆነ እንድንገነዘብ አስረድቶናል። የብርሃኑ ነጋ ገና ቀስተ ደመናን ሲመሰረት ጀምሮ ያሳየው የጠባብነት አቂም ብዙዎቹን ያስደነገጠ ሲሆን ቃሊቲ በነበረበትም ጊዜ ይሁን ከወጣ በኋላ ይህንኑ የጠባብነት አቂሙን በማጠናከር እየሰራ መሆኑን በተግባር እየታየ ነው። ይህ ያው የተለመደና የታወቀ የወያኔ መንገድና ዓላማ ነው። ጸረ አማራነት በቅንጅት ራዕይ ውስጥ ቦታ የለውም። ቅንጅት ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በእኩልነት ማየትና የዘረኝነትን አመለካከት መዋጋትና ማጥፋት እንጂ "አማራም ገዝቷል፣ ትግሬም ገዝቷል፣ ኦሮምም ገዝቷል ጉራጌም መግዛት...." የሚለው የብርሃኑ አባባል አሳፋሪና አሳዛኝ የጥፋት መንገድ ነው። ጥቂት ጓደኞቹን ይስብ እንደሆን እንጂ ሌላውን ኢትዮጵያዊ በዚህ የጠባብነት መንገድ ይከተለዋል የሚል እምነት የለኝም። የእርሱንም ፈለግ በመከተል ብርቱካንም በየስብሰባው የሰው ግንባርና ዓይን እያየች ትግሬዎች የት ገቡ ማለት በመጀመርዋ ነገሩ እንዴት ነው? በማለት ስናጉረመርም ይባስ ብላ ደጋገመችው። እንዲያውም የትግራይን ሕዝብ በይፋ በቅንጅት ስም ይቅርታ በመጠየቋ ሴትዮዋ መንገዷን ፈጽሞ እንደሳተች አስመሰከረች። ለመሆኑ ምን ያህል ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ አማራ ፣ ጉራጌ በአዳራሹ መኖሩን በምን ለየች? ለምንድነው ስለትግራይ ሕዝብ ብቻ በተደጋጋሚ ያስቀረቀራት? ይቅርታም ያስጠየቃት? በዚህም የተነሳ የብርቱካንን ማንነትና እንዴት ወደ ቅንጅት እንደገባች

እንድንጠይቅ አስደርጎናል፡ የዘፈን ዳር ዳሩ እስክስታ ነው አሉ። ምነው ወያኔ ወያኔ ሸተተችሳ? መንገዱን ጨርቅ ያድርግላት።

7ኛ. በውጭው ያለው ኢትዮጵያዊ ነጻነቱን ተገንዝቦ ተቃውሞውን ሲያሰማቸውና እና ፊት ሲነሳቸው ሊመለሱ አንድ ሳምንት ሲቀራቸው መሪያችን ኃይሉ ሻውል ናቸው ችግራችንን በውይይት እንፈታዋል ማለት ጀምረዋል እንዲያውም አስታርቁን ዘመቻ በሽማግሌችና በሃይማኖት አባቶችም በኩል ጀምረው ነበር። በመሰረቱ መታረቅና መስማማት አስፈላጊና የሚደገፍ ነገር ቢሆንም ማጣፊያው ሲያጥርባቸውና ወደ አገር ቤት መመለሳቸውን ሲያስቡትና ፍርሃት ፍርሃት ሲላቸው እንታረቅ ይላሉ። የልባቸውን ሰርተው አሁን የአንድነት ኃይሉ መጠናከርና እውነት እየወጣች ስትመጣ በእርቅ ስም ገብተው እንደገና ሌላ ጥፋት ለመስራት የታቀደ ነገር ነው። የሁለት ዓመት ሴራና ደባ አብቅቶለታል። ከአሁን በኋላ የሚታለል የለም።

8ኛ. አገር ቤት ተመልሰን ቢሮ እንከፍታለን፣ ላዕላይ ምክር ቤት እንሰበስባለን ውሳኔም እንሰጣለን የሚሉት ፈሊጥ ያው እንደለመዱት በግርግር ሩጫ ሴራቸውን ለማከናወን ሲሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የእነብርሃኑ ነጋንና የእነ ብርቱካንን ማንነትና ስራ ጠንቅቆ በማወቁ የእነርሱን አንጃ ቡድን ጨርሶ የማይቀበላቸው፣ ቅንጅት የማይከፋፈል መሆኑን የሚያረጋግጥ፣ የክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልን መሪነት በሙሉ የሚቀበልና የሚደግፍ መሆኑን ካገር ቤት የሚመጡ ዜናዎች ያረጋግጣሉ። ጉድ ፈላባቸው ብርሃኑና ብርቱካን።

9ኛ. ከቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶችና አመራር ጋር ለመነጋገርና ችግር ለመፍታት ያልፈለጉት እነ ብርቱካን ከወያኔ ጋር ለመነጋገርና ለመስራት ችግር እንደሌለባቸው በመደጋገም ተናግረዋል። ከእነ ከሃዲው ልደቱ እና አየለ ጫሚሶ ጋር በስቴት ዲፓርትመንት ያደረጉት ስምምነት የእነ ብርቱካን መንገድ ወዴት እያመራ መሆኑ ግልጽ ነው። ከወያኔ ጋር መስራት። ለብርሃኑ ነጋ ከወያኔ ጋር መሞዳሞዱ አዲስ አይደለምና የለመደበትን የባንዳ ስራ በእነብርቱካን በኩል እያጠናከረው ነው።

10ኛ. በቅንጅት ስም ገንዘብ ከውጭው ነዋሪ ላይ ሰብስበው ለእነርሱ የአንጃ ዓላማ ማስፈጸሚያ የሚያደርጉ ከሆነ በቀጥታ ተጠያቂ የሚያደርጋቸው ስለሆነ የሊቀመንበሩን መመሪያ መቀበል ግዴታ አለባቸው። ያንን ካላደረጉ በሕግም በድርጅትም ደረጃ መጠየቅ ይኖርባቸዋል።

በክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የሚመራው ቅንጅት አንድ እና አንድ ተግባር ብቻ መፈጸም ይኖርበታል እላለሁ። ድርጅቱን የከዱና ከወያኔ ጋር የተሞዳሞዱትን፣ የዘረኝነት መንፈስ ያንጸባረቁትን፣ የድርጅቱን መሪ በሕገወጥ መንገድ ለመገልበጥ የሞከሩትን፣ ለጸረ ኢትዮጵያ ኃይሎች መሳሪያ በመሆን የቅንጅት መሪዎችንና ደጋፊውን ሲከፋፍሉ የነበሩትን እና ለድርጅቱ ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው ያመዘነውን ከቅንጅት ፓርቲ በዲስፒሊን እርምጃ ማስወገድ ብቻ ነው። ባንዳ ተሸክሞ መጓዝ ማብቃት አለበት። ጠላት ምን ጊዜም ጠላት ነው ባንዳም ባንዳ ነው። ወደ ጎራቸው ወደ ልደቱ ካምፕ ይቀላቀሉ። የአንድነት ኃይሉ ትግሉን አጠናክሮ ይቀጥል።

ቅንጅት አይከፋፈልም!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!